ዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴን አውቃቸዋለሁ። በኹለት ድንቅ ሥራዎቻቸው። የመጀመሪያው ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ (አሁን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሚባለው) "ጥንታዊና መካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ" ያስተምሩ የነበረውን ኮርስ ተከታትያለሁ። ረጋ ባለና ጥልቅ በሆነ ኢትዮጵያዊ አቀራረባቸው ልቤ ተነክቶ ዐይኔን የገለጥኩበት ትምሕርት እንደነበር ዘውትር አስታውሳለሁ።

ኹለተኛው "ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ሥልጣኔ መሥራች" (ሙኒክ ጀርመን 1989 ዓ.ም. 479 ገጽ) በሚል ርዕስ የደረሱትን የታሪክ መጽሐፍ አዲስ አበባ ከርቼሌ ወህኒ ቤት በእስር ላይ በነበርኩበት ወቅት ያነበብኩት ነው። መጽሐፉን የሰጡኝ በእስር ቤት አብረን የነበሩት እውቁ የቀዶ ሕክምና ሀኪምና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና መብት ለሀገሪቱ ዳር ድንበር መከበር ተቆርቋሪና ተሟጋች ፕሮፌሰር ዓስራት ወልደየስ አልታዬ ናቸው። ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት አስፈሪ ሁኔታ የበቃችው የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ ቋንቋ ባሕል ሥርዐ-መሠረት ጠንቅቆ ካለመረዳት የተነሳ ብልጣ ብልጥ እብሪተኞችና ተመጻዳቂዎች ያመጡት ጣጣ ነው። ዶ/ር ሥርግው ይህን የእውቀትና የግንዛቤ ጉድለትና ገደል ለማስተካከል እንዲረዳ ከላይ የጠቀስኩትን በምርምርና ጥናት የተመሠረተ መጽሐፍ በስደት በሚኖሩበት ሀገር ጽፈው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቅርበዋል።

የሚያሳዝነውና የሚቆጨው በዶ/ር ሥርግው ጥልቅ እውቀትና የበሰለ አቀራረብ ኢትዮጵያ ሳትጠቀምበት መጽሐፋቸው በብዙ ኢትዮጵያውያን እጅ ሳይገባ ዜና እረፍታቸውን መስማታችን ነው። ይሁንና "ስም ከመቃብር በላይ ይውላል" እንዲሉ የእኚህ ስመ-ጥር ኢትዮጵያዊ የታሪክ ሊቅ ስምና ተግባር በጽሑፎቻቸው ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋሉ።

ወንድአየሁ ካሣ
ዋሽንግተን ዲሲ